
# የውይይት መምሪያ ለቤተሰቦች

Reading Is Fundamental®
until every child reads




**ቼስተር ኔዝ ኤንድ ዘ አንብሬኬብል ኮድ፤ ኤ ናቫጆ ኮድ ቶክስ ስቶሪ (Chester Nez and the Unbreakable Code: A Navajo Code Talker's Story)**

*ደራሲ፤* ጆሴፍ ብሩቻክ (Joseph Bruchac)

*ሰዓሊ (Illustrator)፤* ሊዝ ሆልምስ (Liz Amini-Holmes)

**ይዘቶች(Themes):** አካባቢ እና ዘላቂነት (Environment and Sustainability)

**የመጽሃፉ አጭር መግለጫ (Book Brief)፤** ቼስተር ኔዝ (Chester Nez) በአንድ ወቅት የናቫጆ ስሮቹን እንዲተው ግፊት ሲደረገበት፤ በኋላም አሜሪካ ሁለተኛውን የዓለም ጦርነት እንድታሸንፍ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ተጠቅሟል። እንደ ባህር ሃይልነታቸው፤ እሱ እና ሌሎች  የናቫጆ ሰዎች (Navajo men) የቅርሶቻቸውን ጠቃሚነት የሚያረጋግጥ  የማይሰበር ኮድ ፈጥረዋል።

## ጮክ ብለው ያንብቡ (READ ALOUD)

**ከንባብ በፊት፤ መሰረት ይገንቡ (Build Background)**

- ልጅዎን “አንድ ሰው ሚስጥራዊ ቋንቋ መፍጠር ለምን ያስፈልገው ይመስልሻል?  ሌላ ጠቃሚ ሊሆን የሚችልባቸውን ሁኔታዎች ማሰብ ትችያለሽ? የቼስተር ኔዝ (Chester Nez) ሚስጥራዊ ቋንቋ እንዴት ለውጥ እንዳመጣ ለማወቅ እስቲ እናንብብ” በማለት ይጠይቁ።

**በንባብ ወቅት፤ ግንኙነቶችን ይፍጠሩ (Make Connections)**

- ሚሲዮናዊው ለቤቶሊ (Betoli) ቼስተር (Chester)) ስሙን መቀየር እንደነበረበት እና፤ ይህም ምን ስሜት እንደሚፈጥርበት ለምን የነገረው ይመስልሃል?
- ቼስተር (Chester) እና የክፍል ጓደኞቹ በአዳሪ ትምህርት ቤት እንዴት ይስተናገዱ ነበር? እዚያስ ምን ተፈታታኝ ሁኔታዎች አጋጥሟቸው ነበር?
- በጦርነቱ ወቅት ቼስተር (Chester) ኮድ ለመፍጠር የናቫጆ (Navaj) ቋንቋውን እንዲጠቀም ያነሳሳው ምን ነበር? እናም ይህ የዩኤስ የባህር ሃይል (US Marines) ወታደሮች ድል እንዲቀዳጁ የረዳቸው እንዴት ነው?

**ከንባብ በኋላ፤ ጥያቄዎች ይጠይቁ**

- ቼስተር ኔዝ (Chester Nez) ያጋጠሙትን ተፈታታኝ ሁኔታዎች በጽናት የተወጣው እንዴት ነው? ስኬታማ እንዲሆን የረዱትስ የትኞቹ ባሕርያት ናቸው? በሕይወታችን ውስጥ የሚያጋጥሙንን ችግሮች ለማሸነፍ የእሱ ታሪክ እንዴት ሊያነሳሳን ይችላል?

## ተዛማጅ ተግባራት

**ልጅዎ ይህን መጽሃፍ ከወደደ፤ የሚከተሉትን ከግምት ያስገቡ፤**

- በሌሎች ንግግሮች ጊዜ ስለ እሱ እንዲያወሩ አበረታቷቸው።
- በተዛማጅ መጽሃፍት እና ሪሶርሶች (resources) ስለ ዘላቂነት (sustainability) የበለጠ ለማወቅ የአር አይ ኤፍን (RIF’s) Sustainable Futures ማዕከልን ይመልከቱ።


©2024 Reading Is Fundamental